ረቂቅ

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ማውጫ


የቃላት ፍቺ ..... iii

አሕፅሮተ-ቃላት ..... v

መግቢያ ..... 1

ክፍል አንድ ..... 3

የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማዎች ..... 3

1.1. የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት ..... 3

1.2. መሰረታዊ እሳቤዎች ..... 4

1.3. ራዕይ ..... 5

1.4. ተልዕኮ ..... 5

1.5. ዓላማዎች ..... 5

ክፍል ሁለት ..... 8

የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች ..... 8

2.2 የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ፣ ..... 9

2.2.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 9

2.2.2. ግቦች ..... 9

2.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 10

2.3. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ..... 11

2.3.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 11

2.3.2. ግቦች ..... 11

2.3.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 12

2.4. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ..... 13

2.4.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 13

2.4.2. ግቦች ..... 13

2.4.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 14

2.5. የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት ..... 15

2.5.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 15

2.5.2. ግቦች ..... 16

2.5.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 16


ረቂቅ

2.6. ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ ........ 18
2.6.1. የፖሊሲ መግለጫ ........ 18
2.6.2. ግቦች ........ 18
2.6.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ........ 19
2.7. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ ........ 21
2.7.1. የፖሊሲ መግለጫ ........ 21
2.7.2. ግቦች ........ 21
2.7.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ........ 21
2.8. ሃገራዊ እና ዓለም አቀፍ ትብብር ........ 23
2.8.1. ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት ........ 23
2.8.2. ዓለም አቀፍ ትብብር ........ 26
ክፍል ሦስት ........ 28
የፖሊሲና ስትራቴጂ የአፈጻጸም ማዕቀፍ ........ 28
3.1. አጠቃላይ ምልከታ ........ 28
3.2. ተቋማዊ መዋቅር ........ 28
3.3. የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት ........ 29
3.4. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክትትል እና ግምገማ ........ 29
3.5. የፖሊሲና ስትራቴጂው ህጋዊ ጉዳዮች ........ 30
3.6. የፖሊሲና ስትራቴጂው የፋይናንስ ጉዳዮች ........ 30
3.7. የፖሊሲና ስትራቴጂ ስኬት አመላካቾች ........ 31
3.8. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክለሳ ........ 31

ረቂቅ

# የቃላት ፍቺ

በዚህ ፖሊሲና ስትራቴጂ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፤

**ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች** ማለት ቁልፍ የሆኑ ቁሳዊና ዲጂታል ሀብቶች፣ ኔትዎርኮች፣ አገልግሎቶች እና የመረጃ ስርዓቶችን የሚያካተት ሲሆን፣ ጥቃት ከደረሰባቸው በህዝብ ደህንነትና ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው፡፡

**የሳይበር ምህዳር** ማለት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ መረጃዎች፣ የመረጃ መሰረተ ልማቶች፣ መረጃ ስርዓቶች፣ መረጃን ወደ እውቀት የሚቀይርና የሚጠቀም የሰው ሃይል፤ እንዲሁም ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ባህል ያካተተ ምህዳር ነው፡፡

**ዲጂታል ማንነት** ማለት በሳይበር ምህዳር አማካኝነት ግለሰብ፣ ተቋም ወይም ኤሌክትሮኒክ ቁስ በኦንላይን ወይም በኔትዎርክ አውታሮች ትስስር  የያዘው ማንነት ወይም  አለኝ የሚለው ማንነት ነው፡፡

**ዲጂታል ማንነት ጥበቃ** ማለት የሳይበር ምህዳር ተጠቃሚ ግለሰቦችን፣ ዜጎችን ወይም ተቋማትን የመረጃ ሚስጥራዊነትና ታዓማኒነት መጠበቅ እና ያለፈቃድ አሰሳ (ብርበራ) መከላከል፤ እንዲሁም የጋራ ማንነት ጥበቃን ያካተተ ነው፡፡

**የሳይበር ትንኮሳ** ማለት በይነመረብ እና ተያያዥ ኤሌክትሮኒክ ውጤቶችን በመጠቀም የሚፈጸሙ የትኛውንም ዓይነት ማስፈራሪያ እና መሰል  ድርጊቶችን ያካትታል።

**የሳይበር ወንጀል** ማለት የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችንና ስርዓቶችን በተለይም በይነመረብን በመጠቀም የሚፈጸም ወንጀል ነው።

**የሳይበር ጥቃት** ማለት በሳይበር ምህዳር የሚፈጸም ያለፈቃድ ብርበራ፣ የመረጃ ስርቆት፣ ቫይረሶችን ማሰራጨት፣ ስነ ልቦናዊ ጦርነት እና ሌሎችም የሳይበር ጥቃቶችን ያካትታል።

ረቂቅ

**የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ** ማለት የሳይበር ደህንነትን ለማስተዳደርና ለመምራት የሚያስችል አቅጣጫ ነው።

**የሳይበር ደህንነት ስትራቴጂ** ማለት የፖሊሲው ተልዕኮ፣ ዓላማዎችና ግቦች እንዴት መሳካት እንዳለባቸው የሚያሳይ፤ የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት በስሌት የተዘጋጀ እቅድ፣ ዘዴ እና ተግባር ነው፡፡

**የመረጃ ግላዊነት** ማለት የማንኛውም ሰው መረጃ የመከበርና የመጠበቅ መብት ማለት ነው፤ ይህም መረጃው ከባለቤቱ ፈቃድ ውጪ ተደራሽ ያለመሆን፣ ለሶስተኛ ወገን ተላልፎ ያለመሰጠት፣ የመረጃው ምሉዕነት አለመሸርሸርን ያካተተ ነው፡፡

ረቂቅ

## አሕፅሮተ-ቃላት

| | |
|---|---|
| **ኢኮቴ** | ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ |
| **ኢመደኤ** | ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ |
| **ኢፌዲሪ** | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |

ረቂቅ

# መግቢያ

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለማችን በከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች አማካኝነት እጅግ ፈጣንና ውስብስብ ለውጦችን እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ በተለይም የሳይበር ምህዳር መፈጠር ዓለማችንን ወደ ትንሽ መንደር በመቀየር ሉላዊነትን አስከትሏል፡፡ ሳይበር በዋናነት በኢንተርኔት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ዓለምን በማስተሳሰር ማንኛውም ኢንፎርሜሽን ከየትኛውም የዓለም ጫፍ ተነስቶ በሰከንዶች ውስጥ በመላ ዓለም ላይ እንዲዳረስ አስችሏል፤ የሰዎችን ትስስርና ግንኙነት በቦታና በጊዜ እንዳይገደብ አድርጓል፤ ፈጣን የሆነ የመረጃ ልውውጥን ፈጥሯል፤ እንዲሁም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በመቀየር አጠቃላይ የሰው ልጆችን የኑሮ ዘይቤ ከመሰረቱ ቀይሯል፤ አዲስ የህይወት ምዕራፍን ፈጥሯል፡፡ ምህዳሩ የሰው ልጅን እስከ አሁን ከኖረበት በጊዜና በቦታ የተገደበ አካላዊ ከሆነ የግንኙነትና የኑሮ ዘይቤ አውጥቶ ወደ አዲስና ቨርቹዋል ዓለም አሸጋግሮታል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ከሳይበር ምህዳር ውጪ መሆን የማይቻልበት፤ ያለሳይበር አቅም እንደ ሃገርና ማህበረሰብ ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ ይቅርና ህልውናን ማስጠበቅ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ በሳይበር ምህዳሩ ተወዳዳሪ ያልሆነ ሃገርና ማህበረሰብ ደህንነቱን በፍፁም ማስጠበቅ አይችልም፡፡

የሳይበር ምህዳር ከፍተኛ የደህንነት ስጋት እና አደጋ ያለበት ክልል ነው፡፡ በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሉአላዊነትን ከማስከበር፣ የሰዎች የግል ነጻነትን ከመጠበቅ፤ እንዲሁም ከኢኮቴ ፈጣን እድገት ጋር የተያያዙ ተቃርኖዎች ያሉበት ምህዳር ስለሆነ ደህንነቱን ማስጠበቅ የሁሉም ሃገራት ፈተና ሆኗል፡፡ በመሆኑም ሃገራት የምህዳሩን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፀጋዎችና መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀም የሳይበር ደህንነት ጉዳይን ከኢኮቴ ፈጣን እድገት ትይዩ ለማስኬድ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ እጅግ ከበለፀጉ እስከ በማደግ ላይ ያሉ የዓለም ሃገራት ዘንድም የሳይበር ደህንነት ጊዜ የማይሰጠው ቀዳሚና አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ተከስቷል፡፡

ረቂቅ

ስለሆነም ሃገራት የሳይበር ደህንነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስጠበቅ ከባድ የቤት ሥራ ሆኖባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ የህልውና እንጂ የምርጫ ጉዳይ ስላልሆነ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሃገራት ደህንነቱ የተጠበቀ የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር ሌት ተቀን እየታተሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ብዙ ሃገራት የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ያስችላቸው ዘንድ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያወጣሉ፡፡

ኢትዮጵያ ልክ እንደ ሌሎች ሃገራት ከኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች መስፋፋት ትይዩ የሚከሰቱ እድሎችና የደህንነት ፈተናዎችን እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሃገሪቱ ካለው ውስን ሀብት፣ ከቴክኖሎጂ ጥገኝነትና ከፍተኛ ተጋላጭነት፣ ዝቅተኛ ከሆነው የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና፣ ካለው የባለሙያ እጥረት እና ያልዳበረ የምርምር ሥራ አንፃር  የሳይበር ደህንነት ስጋት እንዲኖር አድርጓል፡፡

ስለሆነም በዘርፉ የሚገኙ እድሎችን አሟጦ ለመጠቀምና ደህንነቱን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ዘመኑን የዋጀ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ በ2004 ዓ.ም የወጣውን የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ በማሻሻል ይህ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

ረቂቅ

# ክፍል አንድ

# የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማዎች

## 1.1. የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት

ፖሊሲና ስትራቴጂው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሊዘጋጅ ችሏል፡-

1. የሳይበር ደህንነት ሁኔታ ከኢኮቴ ፈጣን ዕድገት ጋር ተያይዞ አጠቃላይ መልኩና ባህሪው ከመቀየሩ የተነሳ የአንድን ሃገር ሉአላዊነትና ደህንነት በአግባቡ ማስጠበቅ የማይቻልበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፤ ኢትዮጵያም እጅግ ውስብስብ፣ ተለዋዋጭና ኢ-ተገማች የሆነውን እና በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዘውን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ በርካታ መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም፣ እንዲሁም ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ዘመኑንና ምህዳሩን የሚመጥን ፖሊሲና ስትራቴጂ የሚያስፈልጋት በመሆኑ፤

2. ከመቼውም ጊዜ በላይ የሳይበር ምህዳር በኢትዮጵያ የማህበረ-ባህላዊ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የደህንነት ጉዳዮች ላይ ጉልህ ድርሻ እየያዘና ተጨባጭ ተፅዕኖ እየፈጠረ የሚገኝ በመሆኑ ይህንን ታሳቢ ያደረገ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

3. የሃገሪቱ ኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን የሚከማችበት፣ የሚተነተንበትና የሚሰራጭበት ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና የአሰራር ስርዓቶች ከመስፋፋትና ዲጂታላይዝድ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚመጡ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶችና ጥቃቶች በመጨመራቸው፤

4. የሳይበር ደህንነት በባህሪው የመንግስት ኃላፊነትና ድርሻ ብቻ ተደርጎ የሚወሰድ ባለመሆኑ የመንግስትና የግል ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በዘርፉ የሚኖራቸውን ቅንጅትና አጋርነት ማሳደግ በማስፈለጉ፤

5. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የግሉ ዘርፍ ሊኖረው ከሚችለው ዘርፈ-ብዙ እምቅ አቅም ጋር ተያይዞ በሌላው ዓለም ካለው ተጨባጭ እውነታ፣ እንዲሁም

ረቂቅ

በሃገራችንም ዘርፉ በቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ ያለው ተሳትፎ እያደገ በመምጣቱ  ከመንግስት ተቋማት ጋር የሚኖረውን ተመጣጣኝና ተመጋጋቢ ሚና መምራትና ማስተዳደር በማስፈለጉ፤

6. በዓለም ላይ ከሚስተዋለው የሳይበር ደህንነት ስጋትና ተጋላጭነት አንጻር ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ለማወቅና ለመጠቀም፣ የህግ ማዕቀፎችና የቁጥጥር ስርዓቶች ለመዘርጋት፣ የጥናትና ምርምር አቅም ለመገንባት፣ ንቃተ ህሊናን ለማሳደግ፤ እንዲሁም ወቅታዊና ታሳቢ የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን ከግምት ያስገባ የፖሊሲ አቅጣጫዎችንና ስትራቴጂዎችን መንደፍ እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

## 1.2. መሰረታዊ እሳቤዎች

1. **የመንግስት ቁርጠኛ አመራር**

   የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሀብቶች እና አቅሞች ስምሪት እንዲረጋገጥ ለፖሊሲው አፈጻጸም መንግስት ስትራቴጂክ አመራር ይሰጣል፡፡

2. **የጋራ ኃላፊነት**

   የሳይበር ደህንነት የሁሉም አካላት ኃላፊነት ስለሆነ ዜጎች፣ መንግስት፣ የግሉ ዘርፍ እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በከፍተኛ የባለቤትነት ስሜት ተግባራዊ እንዲሆን በጋራ የሚፈጽሙት ይሆናል፡፡

3. **የህግ የበላይነት**

   የዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብት፣ ነፃነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፤ እምነት የሚጣልበት የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር፤  እንዲሁም በገሃዱ ዓለም ተግባራዊ እንደሚደረገው ሁሉ በከፍተኛ ትስስር ውስጥ ባለው የሳይበር ማህበረሰብ ዘንድም በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ የሳይበር ደህንነትንና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ስራ ቁልፍ ተግባር እንደሆነ ተወስዶ ይተገበራል።

4. **ዓለም አቀፋዊ ትብብርና አጋርነት**

ረቂቅ

የሳይበር ስጋት፣ ተጋላጭነትና ጥቃት ድንበር ተሻጋሪ ባህሪ ያለው በመሆኑ ጠንካራ የሆነ ዓለም አቀፋዊ የትብብርና አጋርነት አቅም ይገነባል፡፡

5. **የኢትዮጵያ እሴቶች**

   የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ እሴቶችን በጠበቀ ሁኔታ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

### 1.3. ራዕይ

ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የማይበገር ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት አቅም ተገንብቶ ማየት፤

### 1.4. ተልዕኮ

የሃገሪቱን ኢንፎርሜሽን እና ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል በራስ አቅም ላይ የተመሰረተ የሳይበር ደህንነት አቅም በመገንባት ብሄራዊ ጥቅሞችን ማስጠበቅ፤

### 1.5. ዓላማዎች

1. የሳይበር ደህንነት ስጋትና ተጋላጭነትን ቀድሞ ለመለየትና ለማስጠንቀቅ፤ እንዲሁም ጥቃትን ለመከላከልና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የማይበገር የሳይበር ደህንነት አቅም ለመገንባት፤
2. የሳይበር ደህንነት በሂደቱና በውጤቱ ለዜጎች የግል ነፃነትና ሰብአዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ እንዲሁም ለዘላቂ ሰላምና ልማት መረጋገጥ ሚና እንዲኖረው ለማስቻል፤
3. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ጠንካራ ሃገራዊ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አጋርነቶችና ትብብሮችን ለመፍጠር፤
4. ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ምርምርና ልማት በማከናወን የቁልፍ መሰረተ ልማቶች እና የኢንፎርሜሽን ሀብቶች ደህንነት በዘላቂነት የሚያስጠብቁ ሃገር በቀል የቴክኖሎጂ አቅሞችን ለመገንባት እና የአሰራር ስርዓቶችን ለመዘርጋት፤

ረቂቅ

5. ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ባህልን በመገንባት፣ ሳይበርን በእውቀት የሚጠቀም ምክንያታዊና የነቃ ማህበረሰብ ለመፍጠር፤

1.6. **መርሆች**

1. **ተጠያቂነት**

ሁሉም የመንግስትና የግል ተቋማት የየራሳቸውን ኢንፎርሜሽን እና የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችንና ስርዓቶችን ደህንነት የመጠበቅ፤ እንዲሁም የሳይበር ምርቶችንና አገልግሎቶችን ደህንነት ባረጋገጠ መልኩ በተጠያቂነት የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡

2. **አይበገሬነት**

በሳይበር ምህዳር የሚኖሩ ተግዳሮቶችን በመቋቋም እና በፍጥነት ከጥቃት በማገገም ይበልጥ ጠንካራና ተጣጣፊ በመሆን የሳይበር ደህንነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

3. **ሉዓላዊነት ተኮር**

ሃገሪቱ በሳይበር ደህንነት ዓለም አቀፋዊ ትብብር፣ ድርድርና ስምምነት ሂደት ውስጥ በምታደርገው ተሳትፎ የሳይበር ሉዓላዊነቷንና ብሔራዊ ጥቅሟን ያስጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4. **ቅንጅትና አጋርነት**

የሳይበር ደህንነትን ማረጋገጥ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ የመንግስትና የግል ተቋማት እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በአጋርነት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

5. **ዓለም አቀፋዊነት**

የሳይበር ደህንነትን የማስጠበቅ ተግባር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከናወን በመሆኑ ዓለም አቀፍ ህጎች፣ መርሆች እና ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መፈጸም ይገባቸዋል፡፡

6. **ሚዛናዊነት**

የሃገርን የሳይበር ደህንነትና የግለሰብ መብትና ነጻነት በጠበቀ መልኩ ይተገበራል፡፡

ረቂቅ

### 1.7. የፖሊሲው ወሰን

ይህ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በሃገሪቱ በሚገኙ በሁሉም በመንግስት፣ በግል እና በሌሎች ተቋማት ላይ የሚተገበር ሲሆን የተቋማቱን ኢንፎርሜሽን፣ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች እና ስርዓቶች፣ እንዲሁም የማንኛውንም ግለሰብ መረጃ ደህንነት ማረጋገጥ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

ረቂቅ

# ክፍል ሁለት

# የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

## 2.1 የፖሊሲ ጉዳዮች

በሳይበር ዓለም የሃገራትን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ፈታኝ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በተለይም ዓለም ዓቀፋዊ ባህሪ ባለው የሳይበር ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ አቅም ያልገነባ ሃገር የሳይበር ሉዓላዊነቱ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ ይህም የሚሆነው በሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ቀዳሚ የሆኑ ሃገራት ቴክኖሎጂውን በቀላሉ አሳልፈው የማይሰጡ ከመሆኑም ባሻገር የቴክኖሎጂው ባህሪ በተፅዕኖ ሥር ለማዋል አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ስለሆነ ነው፡፡ በዚህም በቴክኖሎጂው ወደ ኃላ የቀሩ ሃገራት በእጅጉ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል የሳይበርን ዓለም አለመቀላቀል አማራጭ ባለመሆኑ ሃገራት የዚሁ የሉላዊነት አካል ሆነዋል፡፡ በመሆኑም ሃገራት የዘርፉን ቴክኖሎጂ አቅም ከማጎልበት ጎን ለጎን የቁጥጥር ሥርዓቶችን በማበጀት የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ይጥራሉ፡፡

ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ካሉት ሃገራት ተርታ የምትመደብ ቢሆንም ከሳይበርና ከቴክኖሎጂው ጋር አብሮ ከሚመጣው የደህንነት ተጋላጭነት ማምለጥ አትችልም፡፡ ይህም በመሆኑ የደህንነት ቴክኖሎጂውን በምርምርም ሆነ በግዥ ከመታጠቅ ባሻገር የቁጥጥር ሥርዓት በማበጀት የሳይበርን ጥቃት የመከላከል አቅሟን ማሳደግ ይገባታል፡ ፡ በዚህ ሂደት በሳይበር ዓለም ያሉ ተቃርኖዎችን በመገንዘብ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የሳይበር ደህንነትን ዓለም አቀፋዊና ሃገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ዓበይት የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመለየት ተችሏል፡፡

በመሆኑም ፖሊሲው ሰባት አንኳር የትኩረት አቅጣጫዎችን አካቷል፡፡ እነዚህም ህግና ቁጥጥር፣ ንቃተ ህሊና፣ አቅም ግንባታ፣ ምርምርና ልማት፣ ዲጂታል ማንነትና የግላዊ መረጃ ጥበቃ፣ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ እና ዓለም አቀፍና ሃገራዊ ትብብር ናቸው፡፡

ረቂቅ

## 2.2 የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ፤

### 2.2.1. የፖሊሲ መግለጫ

በአሁኑ ወቅት እየተስፋፋ የሚገኘውን የሳይበር ተጋላጭነትና ስጋት ለመቀነስ፣ ጥቃት ለመከላከል፤ እንዲሁም አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም እና ወቅታዊ የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀትና መተግበር ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በሃገሪቱ ላይ በሳይበር አማካኝነት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን፣ ሽብርተኝነትን፣ ስለላን እና ሌሎች ህገ ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ የሳይበር ደህንነት ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንዳርዶች እና የቁጥጥር ማዕቀፎች ማልማትና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የህግና ቁጥጥር ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች ይነደፋሉ፤ ይተገበራሉ፡፡

### 2.2.2. ግቦች

የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. ሃገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎች እና ስታንዳርዶች ጋር ተጣጣሚነት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ሕግጋት እና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማውጣት፤ በቀጣይነትም ማሻሻል፤

2. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና ሌሎች ህገ ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል እንዲቻል የህግ አካላትን አቅም መገንባት፤

3. በሃገር ውስጥ የሚመረቱና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶችና አገልግሎቶች፤ እንዲሁም ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ዝርጋታ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፍላጎትን ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤

4. ማህበረሰቡ በሃገሪቱ የሳይበር ደህንነት አቅሞች ዙሪያ ያለውን አመኔታ ለማሳደግ በኢንፎርሜሽን አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ስርጭት፣ አጠቃቀም፣ ክምችት

ረቂቅ

እና አወጋገድ ዙሪያ ደረጃቸውን የጠበቁ የህግና ቁጥጥር ማዕቀፎችን መዘርጋት፤

### 2.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. ከሃገራዊ ተጨባጭ የሳይበር ደህንነት ሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙና ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ አስገዳጅ መሰረታዊና የሥነ-ስርዓት ህጎች እና የቁጥጥር ስርዓቶች ማዘጋጀት እና ማሻሻል፤

   **ስልት አንድ፡-** በመንግስት እና በቁልፍ የግል ተቋማት ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ህጎች፣ ስታንደርዶች እና የአሰራር ስርዓቶች ይቀረጻሉ፤ ይተገበራሉ፤

   **ስልት ሁለት፡-** የሳይበር ደህንነት ህግጋትና የቁጥጥር ማዕቀፎች ተቀባይነት እና ተፈፃሚነት ለማሳደግ በሂደቱ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እንዲሰራ ይደረጋል፤

   **ስልት ሶስት፡-** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የህግ ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያግዙ የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፤

2. በሳይበር ደህንነት ህግጋትና ቁጥጥር ማዕቀፎች ዙሪያ ብቁ የህግ አውጪዎችን፣ የህግ አስፈፃሚዎችንና ተርጓሚዎችን በመፍጠር፤ በቀጣይነት አቅም መገንባት፤

   **ስልት፡-** የሳይበር ደህንነት ህጎችን ለማስፈጸም የመርማሪዎች፣ አቃቤ ህጎች፣ ዳኞችና የሌሎች የፍትህ አካላት በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምክክር መድረኮች፣ በኮንፈረንሶችና በመሳሰሉት ዘዴዎች አቅማቸው በቀጣይነት ይገነባል፤

3. ከሳይበር ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ከማቅረብና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ምርቶችን ከማስወገድ ጋር የተያያዙ የጥራትና ቁጥጥር ስታንዳርዶች እና መለኪያዎች መቅረጽ፤

**ስልት፦** በሃገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶች ጥራትና ብቃታቸው ይፈተሻል፤ የፈጻሚ አካሉን አቅም በቀጣይነት የማብቃት ስራዎች ይሰራሉ፤

4. የኢንፎርሜሽን ሚስጢራዊነት፣ ተደራሽነትና ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ ህገ ወጥ የሳይበር ድርጊቶችን ተከታትሎ ለሕግ በማቅረብ መማሪያ ማድረግ፤

**ስልት፡-** ከሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ውሎዎች የማሳወቅ ሥራዎች ይሰራሉ፤

## 2.3. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና

### 2.3.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ደህንነት የቴክኖሎጂ፣ የአሰራር ስርዓትና የሰው ልጅ መስተጋብር ውጤት ሲሆን በተለይም የመንግስትና የግል ተቋማት እና ዜጎች በእውቀትና በአመለካከት ማነስ፤ በተግባር ክፍተት ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነትና ጥቃት ለመከላከል የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ማጎልበት ተገቢ ነው። ስለሆነም በሃገሪቱ የመረጃ ዋጋና የሳይበር ደህንነት ጥቃትን አስመልክቶ በእውቀት ላይ የተመሰረተ የመረጃ ልውውጥ ባህል እንዲገነባ፤ እንዲሁም የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ መንግስት የሚከተሉትን ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶችን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

### 2.3.2. ግቦች

የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የመንግስትና የግል ተቋማት፣ የሙያና ሲቪክ ማህበራት እና ዜጎች በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ያላቸውን እውቀትና አመለካከት ማዳበር፤

2. ከጥንቃቄ ጉድለት፣ ካለማወቅና በቸልተኝነት የሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶች፣ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፤

3. የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችንና ስጋቶችን ለመቀነስ፤ እንዲሁም ጥቃቶችን ለመከላከል እንዲቻል የዜጎችን ንቃተ-ህሊና ማሳደግ፤ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ባህል መፍጠር፤

### 2.3.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ማሳደግ የሚያስችሉ ተቋማዊ መዋቅሮችና የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡-** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማትን መዋቅራዊ ተደራሽነታቸውን በማስፋትና በማጠናከር ለህብረተሰቡ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ይሰጣል፤

    **ስልት ሁለት፡-** በሳይበር ደህንነት ክስተቶች ዙሪያ ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ዘዴዎች በመጠቀም ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች ይሰራሉ፤

    **ስልት ሶስት፡-** በትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ክበቦች ይቋቋማሉ፤

2. በመንግስት እና በግል ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ደረጃቸውን የጠበቁ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት የንቃተ ህሊና ማዕቀፎችና ፕሮግራሞች መቅረጽ፤

    **ስልት አንድ፡-** በሃገሪቱ በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት ዙሪያ የሳይበር ደህንነት ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው የምክክር መድረኮች፣ ውይይቶች እና መሰል የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤

    **ስልት ሁለት፡-** ሃገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ንቅናቄዎች ይካሄዳሉ፤

3. የመገናኛ ብዙሃን የመረጃ ዋጋና መሰረታዊ የሆኑ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ለመፍጠርና ለማሳደግ የሚያስችሉ ስርዓቶች እንዲኖራቸው ማድረግ፤

ረቂቅ

**ስልት አንድ፡-** የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የህብረተሰቡን ንቃተ-ህሊና እና ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፣ ይቀርባሉ፤

**ስልት ሁለት፡-** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ለሚሰሩ መገናኛ ብዙሃን፣ የግል ተቋማት፣ ሲቭክ ማሕበራት እና ለሌሎች አካላት እውቅና እና ማበረታቻ ይሰጣል፤

## 2.4. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ

### 2.4.1. የፖሊሲ መግለጫ

በሃገራችን ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ጠንካራ የሳይበር ደህንነት የአሰራር ስርዓቶችና ተቋማዊ መዋቅሮች ባለመኖራቸው ምክንያት የሳይበር ደህንነት አቅም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህ ምክንያት የሃገሪቱ ዜጎች፣ የመንግስትና የግል ተቋማት ለተለያዩ ጥቃቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ከሳይበር ምህዳር ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ሊያገኙ አልቻሉም። በመሆኑም ጠንካራ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም መገንባት መቻል ለአንድ ሃገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዕድገትና ለውጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ስለሆነ መንግስት በህብረተሰቡ ዘንድ ጠንካራ የሳይበር ደህንነት ባህል ለመገንባት፤ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ለማስፋፋት፤ ተቋማዊ/መዋቅራዊ አቅሞችን ለመገንባት እና የአሰራር ስርዓቶችን ለመዘርጋት፣ እንዲሁም በሃገር ደረጃ የማይበገር እና ተጣጣፊ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም ለመገንባት የሚከተሉትን ግቦች፣ ስትራቴጂዎች እና ስልቶች በማስቀመጥ ይሰራል።

### 2.4.2. ግቦች

የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመለየት እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ መዋቅሮችንና አቅሞችን መገንባት፤

2. የመንግስት፣ የግል እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት አቅማቸውን ማጠናከር፤
3. በሃገር አቀፍ ደረጃ ብቃት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችንና አመራሮችን መፍጠር፤

### 2.4.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. በሃገሪቱ ደረጃውን የጠበቀ የሳይበር ደህንነት ትምህርት እና ስልጠና ፕሮግራም እንዲኖር በማድረግ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ፤ እንዲሁም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዘርፉ የትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርት መቀረፅ፤

    **ስልት አንድ፡-** የሳይበር ደህንነት ትምህርት በሃገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ውስጥ ይካተታል፣

    **ስልት ሁለት፡-** የሳይበር ደህንነት አቅም ለማሳደግ የሚረዳ ወቅታዊ የሆነ የትምህርትና ስልጠና ሰርተፍኬሽን ለባለሙያዎች ይሰጣል፤

    **ስልት ሶስት፡-** የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ሊያሰራ የሚችል የብቃት መመዘኛ ስታንዳርድ ይቀመጣል፤

2. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ውጤታማ እና ብቃት ያላቸው ተቋማዊ አደረጃጀቶችን እና አሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡-** የመንግስትና የግል ተቋማት የሳይበር ደህንነት እውቀት ሽግግርን ለማሳለጥ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች ይተገበራሉ፤

    **ስልት ሁለት፡-** የሳይበር ደህንነት ዕውቀትና ክህሎት ለማዳበር የሚያስችሉ አደረጃጀቶች በመንግስትና በግል ተቋማት ይቋቋማሉ፤ ይተገበራሉ፤

    **ስልት ሶስት፡-** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ስልጠና የሚሰጡ፣ ተስጥኦን የሚያድጉና የሚያበለጽጉ ተቋማት ይቋቋማሉ፤ ነባር ተቋማትም ይጠናከራሉ፤

3. ውጤታማ የሆነ የሳይበር ደህንነት የእውቀት አስተዳደር እና ስርጭት ስርዓት በሃገር ደረጃ መዘርጋት፤

**ስልት አንድ፡-** በመንግስት፣ በግልና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የምርጥ ተሞክሮ፣ የልምድ ልውውጥና፣ የእውቀት ሽግግር ለማድረግ የሚያስችሉ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤

**ስልት ሁለት፡-** የሳይበር ደህንነት እውቀት ሽግግርን የሚያግዙ ቋሚ አውደ ርዕይ ይዘጋጃል፤ ቤተ-መጽሃፍት ይቋቋማል፤

4. ሃገራዊ ጥቅሞችን የሚያስጠብቁ የፈጠራ ችሎታ እና ተሰጥኦን መሰረት ያደረጉ ፕሮግራሞች በመቅረጽ ጠንካራ እና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል መፍጠር፤

**ስልት አንድ፡-** በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት ውስጥ በሚሰሩና አዲስ በሚቀጠሩ ባለሙያዎች ስብዕና እና ተሰጥኦ ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት የማብቃት ስራ ይሰራል፤

**ስልት ሁለት፡-** በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘርፉ ከተሰማሩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር የፈጠራ ችሎታንና ተሰጥኦን የሚያበለጽጉ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤

## 2.5. የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት

### 2.5.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ምህዳር በባህሪው እጅግ ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ እና ኢ-ተገማች በመሆኑ በየጊዜው ከሚመጡ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ተግዳሮቶችን በማጥናት መፍትሄዎችን ማበጀት፤ እንዲሁም በመስኩ ዕውቀት፣ ክህሎት እና ግኝቶችን ለማዳበር ምርምር እና ልማት ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለሆነም የሳይበር መሰረተ ልማቶችንና ቴክኖሎጂዎችን የማበልጸግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግሮች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን የማስፋፋት፤ እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ ያላቸው የምርምር እና ልማት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም መንግስት በዘርፉ ሃገር በቀል የምርምር አቅም እንዲኖር፣ የሳይበር ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ስራዎች በተደራጀ ጥናት እና ምርምር በመደገፍ የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪ ለመገንባት እና በዘርፉ አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ለማድረግ ይሰራል፡፡

ረቂቅ

ይህንን ለማሳካት መንግስት የሚከተሉት ግቦች እና ስትራቴጂዎችን በመለየት ይሰራል፡፡

### 2.5.2. ግቦች

የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፦

1. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምርቶችና አገልግሎቶች በምርምርና ልማት ላይ የተመሰረቱ ማድረግ፤
2. የሳይበር ደህንነት ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች እና ጥቃቶች በጥናትና ምርምር መለየት፤ መፍትሄዎችን ማቅረብ፤
3. የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ሃገር በቀል ዕውቀት እና ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የምርምር እና ልማት አቅም መገንባት፤
4. በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ባህል መገንባት፤

### 2.5.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. ሃገራዊ አሻራ ያለው የሳይበር ደህንነት ምርት እና አገልግሎትን በጥናት እና ምርምር መደገፍ፤

**ስልት አንድ፡-** ምርምርና ልማት የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪውን እንዲመራ የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፤

**ስልት ሁለት፡-** ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ከጥቃት መከላከል የሚያስችሉ በጥናት እና ምርምር የተለዩ ሃገራዊ አሻራ ያላቸው አስፈላጊ ቴክኖሎጂዎች ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ይደረጋል፤

**ስልት ሶስት፡-** አዳዲስ ምርት እና አገልግሎቶች በዘርፉ እንዲበራከቱ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ለማጠናከር የተለያዩ ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፤ ድጋፎችም ይደረጋሉ፤

ረቂቅ

**ስልት አራት፡-** አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ተጨማሪ እሴት ያላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች የሚያቀርቡ የምርምርና ልማት ፕሮግራሞች ይቀረጻሉ፤

2. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በኢንዱስትሪው መካከል ትብብር እና አጋርነት በመፍጠር የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት አቅም መገንባት የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ማስፋፋት፤

**ስልት አንድ፦** የምርምርና ልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል እውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ እና የቴክኖሎጂ አቅም ይገነባል፤

**ስልት ሁለት፦** በተለያዩ የምርምር ተቋማት፣ የደህንነት ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች የሳይበር ደህንነት የልህቀት ማዕከላት እንዳስፈላጊነቱ ይቋቋማል፤

**ስልት ሶስት፦** በሳይበር ምህዳር ውስጥ ባሉ ተዋናዮች መካከል የምርምርና ልማት አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ የእውቀትና የልምድ ልውውጥ መድረኮች፣ ኮንፍረንሶችና ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ፤

**ስልት አራት፡-** የመንግስትና የግል ተቋማት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት ተግባራት ይፈጸማሉ፤

**ስልት አምስት፡-** በሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት አቅም ግንባታ ለሚሳተፉ አካላት የብቃትና ጥራት ደረጃዎችን የሚወስን ስታንደርድ ይወጣል፤

3. የሳይበር ስጋትና ተጋላጭነት ለመቀነስ፣ ጥቃትን ለመከላከል፣ ምላሽ ለመስጠት እና ከጥቃት በፍጥነት ለማገገም እንዲቻል ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በምርምርና ልማት መደገፍ፤

**ስልት አንድ፡-** የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ተጋላጭነትና ጥቃት የመከላከል ተግባር በቀጣይነት በምርምርና ልማት ይደገፋል፤

**ስልት ሁለት፡-** የግል ዘርፉ በሃገሪቱ የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

4. በሃገሪቱ ቅድሚያ በተሰጣቸው ወቅታዊ እና ታሳቢ የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን በጥናትና ምርምር መደገፍ፤

**ስልት አንድ፦** ከቴክኖሎጂው መስፋፋት ጋር ተያይዞ ለሚመጡና በሃገራዊ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ለሚችሉ ስጋቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት የምርምር እና ልማት ተግባራት ይከናወናሉ፤

**ስልት ሁለት፦** በሃገሪቱ ለጥቃት የማይበገር የሳይበር ክልል እና የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪ ግንባታ በጥናትና ምርምር ይደገፋል፤

## 2.6. ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ

### 2.6.1. የፖሊሲ መግለጫ

የዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃዎች ተገቢ የሆነ ትኩረት እና ጥበቃ ካልተደረገላቸው በዜጎች ላይ የሚደርስ የሳይበር ጥቃት እንዲስፋፋ፣ ማንነት ተኮር ጥቃቶች እንዲበራከቱ፣ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ባህልና እሴት ያፈነገጡ ክስተቶች እንዲንሰራፉ በማድረግ የዜጎች የግል ሕይወትና ሰብዓዊ መብቶች ስጋት ላይ እንዲወድቁ ዕድል ይሰጣል። ስለሆነም መንግስት በዜጎች ላይ ያነጣጠሩ የስነ-ልቦና ጥቃቶችን ለመከላከል፣ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የዲጂታል ማንነትና የግላዊ መረጃ ስጋትና ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ እንዲሁም ዜጎች የሚጠቀሟቸውን የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያስችል የሚከተሉትን ግቦች እና ስትራቴጂዎችን ነድፎ ይሰራል።

ረቂቅ

### 2.6.2. ግቦች

የዲጂታል ማንነትና ግላዊ የመረጃ ጥበቃ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. በዜጎች ዘንድ ታዓማኒነት ያለው የዲጂታል አገልግሎት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ፤
2. ታዳጊዎች በኢትዮጵያ ማህረሰብ እሴቶችና በመልካም ስብዕና ታንፀው እንዲያድጉ ሳይበር ሊጫወተው የሚገባውን ገንቢ ሚና በማሳደግ የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን፣ ተጋላጭነቶችንና ጥቃቶችን መከላከል፤

3. በሳይበር አማካኝነት የሚደርስ ጾታዊ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የሥነ-ልቦና ተፅዕኖ መከላከል እና መቀነስ፤
4. ማንነትን መሰረት ያደረጉ በዲጂታል የሚፈጸሙ የሃይማኖት፣ የብሔር እና ሌሎች ወገን ተኮር ጥቃቶችን መከላከል፤

### 2.6.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ለመጠበቅ የሚያስችሉ አስገዳጅ የህግ ማዕቀፎች ማዘጋጀት እና የቴክኖሎጂ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት፤

   **ስልት አንድ፡-** የግላዊ መረጃ ደህንነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ ማዕቀፎች ይዘጋጃሉ፤ በቅንጅት ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

   **ስልት ሁለት፡-** የመረጃ የግል ሕይወት መብትን የማይጥስ የሳይበር ደህንነት አዳዲስ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የቁጥጥር አሰራሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

   **ስልት ሶስት፡-** የግል መረጃ አሰባሰብ፣ አሰራር እና መቆጣጠሪያ መመሪያ ይዘጋጃል፤

   **ስልት አራት፡-** የሳይበር ደህንነትን በማረጋገጥ ሂደት የግላዊ መረጃ ጥበቃ ተግባር ሚዛናዊነትን ጠብቆ እንዲከናወን ይደረጋል፤

2. የመንግስት ኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤

   **ስልት አንድ፡-** በየተቋማቱ የግለሰቦች መረጃ በሚሰበሰብበት፣ በሚከማችበትና አገልግሎት ላይ በሚውልበት ወቅት ከግለሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው መብትና ግዴታ የሚያመላክት ግላዊ መረጃ ጥበቃ ስምምነት ይደረጋል፤

   **ስልት ሁለት፡-** ተቋማት የግለሰቦችን የግል ሕይወት መብት መጠበቅ የሚያስችል አሰራር በሚያወጧቸው የሳይበር ደህንነት መመሪያዎች እና ሌሎች የአሰራር ስርዓቶች እንዲያካትቱ ቁጥጥር ይደረጋል፤

ረቂቅ

**ስልት ሶስት፡-** የግለሰቦችን ግላዊ መረጃ ጥበቃ በተመለከተ በየተቋማቱ በቀጣይነት የክትትል እና የትንተና ስራ ተግባራዊ ይደረጋል፤

3. በሳይበር የሚፈፀሙ በማንነት ላይ ያተኮሩ የሃይማኖትና የብሔር ማጥላላት እና መሰል ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡-** በሳይበር አማካኝነት የሚደረግ የጥላቻ ንግግር እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የሚከለክል፤ አግባብነት ያለው የሳይበር ደህንነት አጠቃቀም የሚያበረታታ ደንቦችና አሰራር ስርዓቶች ይተገበራሉ፤

    **ስልት ሁለት፡-** በሳይበር አማካኝነት የሚፈጸሙ የጥላቻ ንግግሮችና ሃሰተኛ ዜናዎችን ለመለየትና ለመከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ አሰራር ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

4. በሳይበር ምህዳር የታዳጊዎችን መልካም ስብዕናና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፤ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡-** የታዳጊዎች የዲጂታል መብት ጥሰት ለመከላከል የሚያስችል ክትትል ይደረጋል፤

    **ስልት ሁለት፡-** ተቋማት የታዳጊዎችን ዲጂታል መብት በጠበቀ መልኩ ተግባራቸውን ያከናውናሉ፤

    **ስልት ሶስት፡-** በሳይበር ምህዳር የሚሰራጩ ከማህበረሰቡ እሴት ያፈነገጡና በታዳጊዎች ላይ ያነጣጠሩ መልዕክቶችን ለመከላከል የሚያስችል ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

5. ተቋማት በሴቶችና ታዳጊዎች ዲጂታል ማንነት ጥበቃ ዙሪያ ፕሮግራሞች ቀርፀው እንዲንቀሳቀሱ ድጋፍ ማድረግ፤

    **ስልት አንድ፡-** በሴቶችና ታዳጊዎች የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ጥበቃ ለማጠናከር የሚያስችሉ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ይዘጋጃሉ፤

    **ስልት ሁለት፡-** በሴቶችና ታዳጊዎች የዲጂታል ግል ህይወት መብት ጥበቃ ዙሪያ የምክክር መድረኮች ይመቻቻሉ፡፡

    **ስልት ሶስት፡-** የሳይበር ምህዳርን በመጠቀም በሴቶች ላይ የሚደርሱ የስነልቦና ጥቃቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፤

ረቂቅ

## 2.7. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ

### 2.7.1. የፖሊሲ መግለጫ

በአሁኑ ጊዜ ኢንፎርሜሽን ውድ ሃብት እየሆነ በመምጣቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን ከሳይበር ጥቃት መከላከል፣ ስጋትና ተጋላጭነትን መቀነስ፣ ጉዳት ሲደርስ በፍጥነት መልሶ ማቋቋም ተገቢ ነው። የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እና ተዓማኒነትን ለማሳደግ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ መንግስት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት ይሰራል፡፡

ስለሆነም መንግስት በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ የሳይበር ክስተቶችንና ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ከግሉ ዘርፍ ጋር በቅንጅትና በአጋርነት በመስራት የሃገሪቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር እንዲቻል የሚከተሉትን ግቦች እና ስትራቴጂዎች በመንደፍ ይሰራል።

### 2.7.2. ግቦች

ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች እና ተቋማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን የመለየት፣ የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት አቅም ማጎልበት፤
2. ከውጭ የሚገቡ እና በሃገር ውስጥ የሚመረቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ምርቶችና አገልግሎቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤
3. ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ መካከል ቅንጅት እና አጋርነት መፍጠር፤

### 2.7.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች እና ተቋማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን መለየት፤ መከላከል እና ምላሽ

መስጠት የሚያስችሉ ተቋማዊ መዋቅሮችና አቅሞች መገንባት፤ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

**ስልት አንድ፡-** ቁልፍ የመንግስትና የግል ተቋማትን ሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፤

**ስልት ሁለት፡-** በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጥቃት የሚለይና አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥ አካል ይቋቋማል፤

**ስልት ሶስት፡-** ሃገራዊ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ደህንነት አመራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ቀጣይነት ባለው መልኩ ይሻሻላል፤

2. በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ደረጃቸውን የጠበቁ የቁጥጥር ስርዓቶችን ለማልማት የሚያስችል አቅም መገንባት፤

**ስልት አንድ፡-** የመንግስት እና የግል ተቋማት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና ሃገራዊ አውድ ያገናዘቡ የሳይበር ደህንነት ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስታንዳርዶችና፣ ማዕቀፎች ስራ ላይ ያውላሉ፤

**ስልት ሁለት፡-** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት ዓለም አቀፍ ይዘት ካላቸውና ከሃገሪቱ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስታንዳርዶችና የአሰራር ሥርዓቶች ጋር የተጣጣሙ መርሃ-ግብሮች እንዲቀርፁና የስራ ሂደቶቻቸው አካል እንዲያደርጉ ይደረጋል፤

**ስልት ሶስት፡-** ለሚመለከታቸው አካላት በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶችን፣ ተጋላጭነቶችን፣ ጥቃቶችንና ውድመቶችን ለመለየት፣ ለመከላከል እና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉና ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ ትምህርቶች፣ ስልጠናዎች እና የምክክር መድረኮች ይዘጋጃሉ፤

**ስልት አራት፡-** ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ደህንነት የሚውሉ ሃገር በቀል ምርቶችና አገልግሎቶች የማምረትና የማቅረብ አቅም ይገነባል፤

ረቂቅ

3. ደህንነታቸው የተረጋገጡ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ የመገናኛ ዘዴዎች፣ አስተማማኝ አውታረ-መረቦች እና የቴክኖሎጂ ቁጥጥር ሥርዓቶች ማልማት፤

**ስልት አንድ፡** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች፣ የኢኮቴ ምርቶች እና አገልግሎቶች ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ስታንደርድ ስራ ላይ ይውላል፤

**ስልት ሁለት፡-** በማንኛውም ጊዜ የኢንፎርሜሽንና የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት ዳሰሳ፣ ዘልቆ የመግባት ሙከራ እና የሳይበር ደህንነት ኦዲት እንዲካሄድ እና ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፤

4. ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የመንግስት፣ የግል ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሚና ማሳደግ፤

**ስልት አንድ፡-** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን በየጊዜው በመለየት ሚናቸውንና ድርሻቸውን ለማስቀመጥ የሚያስችል መስፈርት ይዘጋጃል፤ ይተገበራል፤

**ስልት ሁለት፡-** ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችና ስርዓቶች 24/7 አካላዊና ቨርቹዋል ጥበቃ ይደረጋል፤

**ስልት ሶስት፡-** ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተግባሮችና ኃላፊነቶች ተለይተው ይቀመጣሉ፤

## 2.8. ሃገራዊ እና ዓለም አቀፍ ትብብር

### 2.8.1. ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት

#### 2.8.1.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ደህንነት ጥቃት እጅግ ውስብስብ፣ ኢ-ተገማች፣ ተለዋዋጭና ድንበር የለሽ ከመሆኑ የተነሳ በመንግስትና በተወሰኑ ተቋማት ብቻ መፍትሄ የሚገኝለት ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት መመስረት፤ እንዲሁም በሳይበር ደህንነት ላይ የተጋረጡ ስጋቶችን መከላከል የሁሉም የባለድርሻ አካላት የጋራ ኃላፊነት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተለይም የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ልማት በወሳኝነት የግሉን ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ

ይፈልጋል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግሉ ዘርፍ በሀገሪቱ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ ዕድገት በማሳየት ላይ ቢሆንም የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪውን ከማሳደግ አንጻር ያሉ ለውጦች ውስን በመሆናቸው የግሉ ዘርፍ ሀገሪቱ በሳይበር ደህንነት የምታደርገውን ጥረት በማፋጠን ረገድ ቁልፍ ሚና መጫወት እንደሚገባው መንግስት ይገነዘባል። ስለሆነም በሃገር ደረጃ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ሃገራዊ አቅሞችን አስተባብሮ በመጠቀም፣ እንዲሁም የግሉን ዘርፍ አስተዋጽኦ በማሳደግ ረገድ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚከተሉትን ግቦችና ስትራቴጂዎች በማስቀመጥ ይሰራል፡፡

#### 2.8.1.2. ግቦች

ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. ሃገራዊ ሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍ እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅትና አጋርነት መመስረትና ማጠናከር፤
2. የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ሃገር በቀል የግል ተቋማት በሃገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤

#### 2.8.1.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. በሃገራዊ ሳይበር ደህንነት ቁልፍ ሚና ባላቸው የመንግስት እና የግል ዘርፍ አካላት መካከል የቅንጅትና የአጋርነት ሥርዓት መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡-** የሳይበር ደህንነት ቅንጅትና እና አጋርነት የሚመራ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ይደረጋል፤

    **ስልት ሁለት፡-** ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ቅንጅትና አጋርነትን የሚያጠናክሩ ፕላትፎርሞች ይቋቋማሉ፤ በቀጣይነትም በሃገር ደረጃ በየጊዜው ይዘጋጃሉ፤

2. ዜጎች፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማህበራትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል፤

ረቂቅ

**ስልት አንድ፡-** በባለድርሻ አካላት ዘንድ የድርሻና ኃላፊነት ግልጽነት ይፈጠራል፤

**ስልት ሁለት፡-** በሳይበር ደህንነት ባለድርሻ አካላት መካከል የልምድ ልውውጥና የዕውቀት ሽግግር ይደረጋል፤

3. የድንገተኛ ኮምፒውተር አደጋዎች መከላከል ቡድን/ክፍል በሁሉም የመንግስት እና የግል ተቋማት መካከል የሳይበር ደህንነት አገናኝ ድልድይ ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል፤

**ስልት አንድ፡-** የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋዎች መከላከል የሥራ ክፍል እንዲኖራቸውና በክስተቶች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ይደረጋል፤

**ስልት ሁለት፡-** የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋዎች መከታተያ ሥርዓታቸው ከብሄራዊ የኮምፒውተር አደጋዎች መከታተያ ሥርዓት ጋር የተቀናጀ እና የሚመጋገብ ይደረጋል፤

4. በሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪ ግንባታ መስክ ሃገር በቀል የግል ዘርፍ ተሳትፎና አስተዋጽኦ እንዲጨምርና እንዲጠናከር የሚያስችል የቅንጅትና አጋርነት ሥርዓት መዘርጋት፤

**ስልት አንድ፡-** አዳዲስ ተቋማት እንዲፈጠሩና ያሉት ተቋማት እንዲጠናከሩ የሚያግዙ መርሃ ግብሮች ይቀረጻሉ፤ ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

**ስልት ሁለት፡-** ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ የሳይበር ደህንነት ውጤቶችን ለሚያመርቱ አካላት የማበረታቻ ስርዓት ይዘጋጃል፤

**ስልት ሶስት፡-** ደረጃቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎቶች በሃገሪቱ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉበት የድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት ይመቻቻል፤

**ስልት አራት፡-** የግል ዘርፍ በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆን ትኩረት በመስጠት ይሰራል፡፡

ረቂቅ

### 2.8.2. ዓለም አቀፍ ትብብር

#### 2.8.2.1. የፖሊሲ መግለጫ

ከሳይበር ደህንነት ተለዋዋጭነትና ድንበር የለሽነት ባህሪይ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስጋቶችን፣ ተጋላጭነቶችንና ጥቃቶችን ለመከላከል ሃገራት የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንደርዶች፣ ልምዶች እና አመለካከቶች አሏቸው፡፡ ይህ በራሱ አንድ እርምጃ ቢሆንም በሃገራት መካከል በመስኩ ትብብር የማይኖር ከሆነ ደህንነቱን በሚፈለገው ደረጃ ማስጠበቅ አዳጋች ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሃገራት  የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመከላከል፣ የደህንነት ሁኔታን ለማጎልበት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር ዓለም አቀፍ ትብብር የማድረግ ዝንባሌ ይታያል፡፡ ስለሆነም መንግስት ይህንን እውነታ በመገንዘብ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል እንደ የሳይበር ሽብርተኝነት፣ የሳይበር ስለላ፣ እና መሰል ድንበር ተሻጋሪ የተቀናጀ የሳይበር ወንጀሎችን ለመከላከል ይረዳ ዘንድ ዓለም አቀፍ ትብብር እንደ ፖሊሲ ትኩረት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

#### 2.8.2.2. ግቦች

የዓለም አቀፍ ትብብር የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ድንበር ተሻጋሪ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ለመከላከል ትብብር መፍጠር፤
2. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር የሃገሪቱ የሳይበር ዲፕሎማሲ አካል እንዲሆን ማድረግ፤
3. ሁለትዮሽና ከዚያ በላይ በሆኑ ሃገራት መካከል የሳይበር ደህንነት ስምምነቶችን ማበረታታት እና ማጎልበት፤

#### 2.8.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ድንበር ተሻጋሪ የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን በመከላከል ዙሪያ የሚፈጠሩ የህግ ጥያቄዎችን ለመፍታት የሚያስችል የትብብር አሰራር ስርዓት መዘረጋት፤

**ስልት አንድ፡-** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚኖሩ ዓለም-አቀፋዊ የትብብርና የአጋርነት ስምምነቶች ይደረጋሉ፤

2. ድንበር ተሻጋሪ የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል በቴክኒካል እና በሕግ ማዕቀፎች የተቃኘ ዓለም አቀፍ ትብብሮች መመስረት፤

    **ስልት አንድ፡-** የሳይበር ጥቃቶችን ለመመከት ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግባቸው መንገዶች ይመቻቻል፤

    **ስልት ሁለት፡-** ከሃገራት ጋር የመረጃ ልውውጥ እና የቴክኒካል ትብብርና ድጋፍ ይደረጋል፤

    **ስልት ሶስት፡-** የሳይበር ደህንነትን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ አካል ሆኖ እንዲሰራበት ይደረጋል፤

3. ዓለም-አቀፍ የልምድ ልውውጥና የእውቀት ሽግግርን የሚያፋጥን ሥርዓት መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡-** ዓለም አቀፍዊ፣ አህጉራዊና ቀጠናዊ ስምምነቶችና ድርድሮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶች ይሰራሉ፤

    **ስልት ሁለት፡-** የግልና የመንግስት ተቋማት ከሌሎች ሃገራት መንግስታትና የግል ተቋማት ጋር ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ቁርኝት ተገቢ በሆነ መልኩ እንዲያጠናክሩ ሁኔታዎች ይመቻቻል፤

    **ስልት ሶስት፡-** በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ላይ ብቃት ያለውን የሰው ኃይል ለመፍጠር ዓለም አቀፍ ስልጠናዎች ይመቻቻሉ፤

4. በሃገሪቱ ውስጥ የሚቀረጹ የሳይበር ደህንነት ህጎችና ፖሊሲዎች ዓለም-አቀፍ ይዘት ካላቸው የህግ ማዕቀፎችና ስታንዳርዶች ጋር ማጣጣም፤

    **ስልት አንድ፡-** ዓለም-አቀፍ በሆኑ የሳይበር ደህንነት ትብብር መድረኮች ላይ የሃገሪቱን ፍላጎት በጠበቀ መልኩ ንቁ ተሳትፎ ይደረጋል፤

    **ስልት ሁለት፡-** ሃገሪቱ የፈረመቻቸውና ያጸደቀቻቸው ተያያዥ ዓለም አቀፍ ህጎች እና በዘርፉ ያሉ አዝማሚያዎች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያዝ ይደረጋል፤

ረቂቅ

# ክፍል ሦስት

## የፖሊሲና ስትራቴጂ የአፈጻጸም ማዕቀፍ

### 3.1. አጠቃላይ ምልከታ

ይህንን ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ለማስፈፀም የተቋማት ድርሻና ኃላፊነት መለየት፣ አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ አወቃቀሮችን መፍጠር፣ የክትትልና ግምገማ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤ እንዲሁም የወደፊት አቅጣጫ ማመላከት አስፈላጊ ነው። የሳይበር ደህንነት በባህሪው ውስብስብና እጅግ ተለዋዋጭ በመሆኑ ከዘርፉ ደህንነት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ተግዳሮቶችን አንድ አካል ለብቻው መወጣት ይቸግረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በአጋርነት መስራት ያስፈልጋል። ስለሆነም የሳይበር ደህንነት ፖሊሲው ውጤታማ እንዲሆን የመንግስት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ስትራቴጅካዊ አመራር ይሰጣል።

### 3.2. ተቋማዊ መዋቅር

በሃገራችን የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ ቁመና ያላቸው ተቋማት መፍጠርና ያሉትንም ማጠናከር ያስፈልጋል። መንግስት ይህንን በመገንዘብ ኢ.መደኤን ያቋቋመ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግስት በሃገር ደረጃ እና በቁልፍ ተቋማት የሚከሰቱ የሳይበር ደህንነት ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያገለግል ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ጥቃት የሚከላከል አካል (ኢትዮ ሰርት) በማቋቋም የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል።

የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ከተለያዩ ሃገራዊ ተቋማት ጋር በትብብርና በአጋርነት መስራት አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ትብብርና አጋርነት ውጤታማ እና የተቀናጀ ለማድረግ ተቋማዊ መልክ በማስያዝ የሚመለከታቸውን የመንግስት፣ የግል እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት ይቋቋማል። መንግስት ለፖሊሲው አፈፃፀም በሚያመች ሁኔታ በሃገር ደረጃና በዘርፍ ደረጃ አዳዲስ

ተቋማትን እና ግብረ ኃይሎችን ሊያቋቁም ወይም ባሉት ተቋማት ላይ ኃላፊነት ሊጨምር ይችላል። እንዲሁም ተቋማዊ መዋቅሩ ይህንን ፖሊሲና ስትራቴጂ ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ የግሉን ዘርፍ ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ይዘረጋል፡፡

### 3.3. የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት

ሁሉም የመንግስት፣ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ያላቸው የግል ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ይህንን ፖሊሲና ስትራቴጂ መተግበር አለባቸው። በተጨማሪም ከዚህ ፖሊሲና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች ጋር የሚጣጣም የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች የመንደፍና የመተግበር ኃላፊነት አለባቸው።

### 3.4. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክትትል እና ግምገማ

የፖሊሲና ስትራቴጂውን ውጤታማነት በሁሉም ደረጃ ለመለካት እንዲቻል፤ እንዲሁም የፖሊሲውን አፈፃፀም ሂደት ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ዓበይት ጉዳዮች ያካተተ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

1. የፖሊሲውና ስትራቴጂው ማስፈጸሚያ የድርጊት መርሃ ግብር በኢመደኤ ይዘጋጃል፤ ለአፈጻጸሙም የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት የሚጠበቅበትን ሚና ይጫወታል፣
2. የመንግስትና የግል ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በፖሊሲና ስትራቴጂው የተጠቀሱና የሚመለከታቸው ተግባሮችን፣ እንዲሁም ፖሊሲና ስትራቴጂውን ለመተግበር በሚዘጋጁ ማዕቀፎች የሚካተቱ ተግባሮችን ማከናወናቸውን፣ አስፈላጊው ተቋማዊ መዋቅር መዘርጋቱን እና አስፈላጊው በጀትና ግብአት መመደቡን የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
3. በኢመደኤ አስተባባሪነት የፖሊሲና ስትራቴጂ አፈጻጸም ዙሪያ ኢንፎርሜሽን የማሰባሰብ፣ የማደራጀትና የመተንተን ተግባር ይከናወናል፤ እንዲሁም የሪፖርት ሥርዓት ይዘረጋል፤



ረቂቅ

4. የፖሊሲውንና ስትራቴጂውን አፈጻጸም ለመገምገም የሚረዳ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ አመታዊ ጉባዔ በኢ.መደኤ ይዘጋጃል፤
5. በሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራተጂ ክትትልና ግምገማ ውጤት መሰረት ሌሎች አስፈላጊ ማዕቀፎች የሚዘጋጁበት እና እንደ አስፈላጊነቱ ፖሊሲና ስትራቴጂው የሚሻሻልበት አቅጣጫ ይቀመጣል፤

## 3.5. የፖሊሲና ስትራቴጂው ህጋዊ ጉዳዮች

7. ይህ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በተወካዮች ምክር ቤት ሲፀድቅ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
8. ፖሊሲና ስትራቴጂው በሁሉም በዚህ ሰነድ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተመላከቱ አካላት ላይ ህጋዊ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡
9. ይህንን ሃገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተፈጻሚ በማያደርጉ አካላት ላይ ተጠያቂ የሚያደርግ ህግ እንደአስፈላጊነቱ ይወጣል፡፡

## 3.6. የፖሊሲና ስትራቴጂው የፋይናንስ ጉዳዮች

1. ፖሊሲና ስትራቴጂውን ተፈጻሚ ለማድረግ እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅም በዋነኝነት ከመንግስት በሚመደብ በጀት ይሸፈናል፡፡

2. ለፖሊሲና ስትራቴጂው ማስፈጸሚያ የሚውለው በጀት በፖሊሲ ሰነዱ በተቀመጠው የክትትልና ግምገማ ስርዓት መሰረት ይህንን ፖሊሲ በበላይነት እንዲከታተል በህግ ሃላፊነት የተሰጠው አካል ውሳኔ መሠረት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

3. የፖሊሲውን ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች ለማስፈጸም የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች እንደአስፈላጊነታቸው በሚመለከታቸው አካላት ትብብር የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡

ረቂቅ

### 3.7. የፖሊሲና ስትራቴጂ ስኬት አመላካቾች

1. የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ተከትሎ የሚመጡ ጉዳቶች በመቀነስ የተረጋጋ ማህበረ-ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች፤
2. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተገነቡ ሃገራዊ፣ ዘርፋዊ እና ተቋማዊ አቅሞችና ስርዓቶች፤
3. በሃገራዊ አቅም የቀረበ የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎቶች፤
4. ሳይበርን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መጠቀም የሚችል የነቃ ማህበረሰብ መፈጠር፤ እንዲሁም በሀገሪቱ የተገነባ የሳይበር ደህንነት ባህል፤
5. የግሉን ዘርፍ ባሳተፈ መልኩ የተገነባ የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪ፤
6. ያደገና ተጨባጭ ብሔራዊ ጥቅም ያስገኘ ሃገራዊ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሳይበር ደህንነት አጋርነቶች እና ትብብሮች፤

### 3.8. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክለሳ

በሃገሪቱ ከሚከሰቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ቴክኖሎጂያዊ ለውጦች ጋር ተያይዞ በሳይበር ደህንነት አጠባበቅ ሂደት ላይ በሚኖረው ተጽዕኖ፤ በዘርፉ የመንግስትና የግል ተቋማት ድርሻና ኃላፊነት እድገት ተከትሎ በሚፈጠሩ አዳዲስ ፍላጎቶች፤ እንዲሁም በፖሊሲው የክትትልና ግምገማ ውጤት መሰረት በሚሰጠው አቅጣጫ ይህ ፖሊሲና ስትራቴጂው ሊሻሻል ይችላል። በእነዚህ እይታዎች መነሻ የብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ጸድቆ ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ፖሊሲው ይከለሳል። የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት የፖሊሲውን ክትትልና ግምገማ ውጤት መነሻ በማድረግ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሰረት ኢመደኤ የፖሊሲና ስትራቴጂውን ክለሳ ሂደት የመምራትና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።

ረቂቅ